መመሪያ አንድ፡- ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የያዘውን ፊደል መርጠህ/ሽ በመልስ መስጫ ላይ አጥቁር/ሪ።

1. ገሰፀ፡-

A. ገረሰሰ C.አባረረ

B. ተቆጣ D. ፈራ

2. ይሻል፡-

A. ይፈልጋል C. ያማርጣል

B. ያወዳድራል D.ያሻሽላል

3. ውጥን፡-

A. ያለቀ C.ጅምር

B. የተጠናቀቀ D. ጥንቃቄ

4. ማላገጥ፡-

A. ማንጋጠጥ C. ማስረዳት

B. ማሾፍ D. ማዋሃድ

5. ሳይታክት፡-

A. ሳይበሳጭ C. ደከመኝ ሳይል

B. ሳይሰራ D. ሳይመለከት

መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቀራኒ ፍቺ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሺ

6. ተደሰተ፡-

A. ፈነጠዘ C. አስከፋ

B. ፈነጣጠዘ D. ተከፋ

7. ገሃድ፡-

A. ሩቅ C.ድብቅ

B. ቅርብ D.ግልፅ

8. ንፉግ፡-

A. ጨካኝ C. ክፉ

B. ቸር D. ንዝላል

9. ጠረጠረ፡-

A. አመናታ C.አመነ

B. ካደ D.ፈለፈለ

10. ተቃወመ፡-

A. አወላወለ
C. ነቀፈ
B. ደገፈ
D. ነቃ

መመሪያ ሦስት፡- ቀጥሎ በቀረቡት 0 .ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም ሐረጎች አገባባዊ ትርጉም ምረጥ/ጪ

11. መምህሩ ተማሪውን **<u>በፈገግታ</u>** ተቀበለው

A. በግድየለሽነት
C. በደስታ
B. በቁጣ
D. በይሉኝታ

12. በሰፈራችን የተፈጠረውን አደጋ ሲሰማ **<u>ከውአለ፡፡</u>**

A. ተዝለፈለፈ
C. ደነገጠ
B. አዘነ
D. ዝም አለ

13. ሰውዬው የያዘው ዱላ **<u>ገዳዳ</u>** ነው፡፡

A. ቀጥያለ
C. ቀጭን
B. ጠንካራ
D. ጠማማ

14. ግቢውን **<u>አፅድታችሁ</u>** ጠብቁኝ፡፡

A. ሙሉ አድርጋችሁ
C. ንፁህ አድርጋችሁ
B. ባዶ አድርጋችሁ
D. አስፍታችሁ

15. ሲካሄድ የነበረው ስብሳባ **<u>ተደናቀፈ</u>፡፡**

A. ተካሄደ
C. ተሳካ
B. ተቋረጠ
D. ተሰናከለ

መመሪያ አራት፡- በትዕዛዙ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

16. ደነቆረ ብሎ ድንቁርና ካለ ፈለሰፈ ብሎ_____ ይላል፡፡

A. ተፈላሰፈ
C. ተፈላሰፊ
B. ፍልስፍና
D. ይፈላሰፋል

17. ቅጥያ የሌለው ቃል የትኛው ነው?

A. ዘማኞች
C. ቅርስ
B. ቀጥተኛ
D. ስለሚመጣ

18. ድርብ ቃል ያልሆነው የትኛው ነው?

A. መሠረተ ትምህርት
C.መልክአምድር
B. አመለወርቅ
D.ከነመፍትሄው

19. አረፍተ ነገር ያልሆነው የትኛው ነው?

A. ልብሱን ለበሰ
C.ልብሱን ለብሶ
B. እየሮጠ ሄደ
D. ፀጉሩን አበጠረ

20. «ለውሻው» የሚለው ቃል ቅጥያዎች

A. ለ-
C. ውሻ
B. -ው
D. ለ- እና -ው

21. በሐኪም የታዘዘለትን መድሃኒት እየወሰደ ነው፤_____ እስካሁን አልተሻለውም፡፡

A. ስለሆነም
C.ስለዚህ
B. ይሁን እንጂ
D. ባይሆንም

22. ወደ ቤቱ_____ ኖሮ አገኘው ነበር፡፡

A. ስለመጣ
C. ሲመጣ
B. ቢመጣ
D. ከመጣ

23. ተግባርህን በብቃት_____ አለብህ፡፡

A. ማለፍ
C. ማዝረክረክ
B. ማሰብ
D. መወጣት

24. የከበደ ወንድም የተሸለመው አንደኛ_____ ነው

A. ቢወጣ
C. ስለወጣ
B. ከውጣ
D. ለወጣ

25. የአረፈተ ነገር አወቃቀር ስረዓትን የተከተለው የትኛወ ነው?

A. የተተከሉት አበቦች ስላ ደገ አከባቢው አሸበረቀ፡፡
B. ስፖርት ስለምትሰራ ሰውነቱ ጠንክሯል፡፡
C. ፍላጎቷ ስለተሳካለት በጣም አዝናለች፡፡
D. ዝናብ ስለዘነበ አካባቢው ጨቀየ፡፡

26. የደበላ በቅሎ_____

A. ትሸከርከራለች
C. ትሰግራለች
B. ትከንፋለች
D. ትሮጣለች

27. በቆሎ ዘራ ካለ ችግኝ _____ ይላል፡፡

A. ቸከለ
C. አበቀለ
B. ተከለ
D. በተነ

28. ለአከለ መጠን_____

A. ደረሰ C.አደገ

B. ሆነ D.ተዘጋጀ

29. ዝናብ ስላልጣለ_____

A. መኪናው በጭቃ ይያዘል C.መንገዱ ሁሉ ጨቀየ

B. መንገዱ አቧራ ይሆናል D.መኪና በጭቃ ይያዘል።

30. መኪናው ቤንዚን ሰለጨረሰ_____

A. በፍጥነት እየበረረ ነው C.መቆሙ አይቀርም

B. ጎማው ቀነሰ D. አይቆምም

መመሪያ አምስት፡- ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዐ.ነገሮች ተስማሚውን ስርዓተ-ንጥብ በመምረጥ መልስ/ሽ

31. ውይ _____ ስልኬን ጣልኩ።

A. ፤ C. ፥

B. ! D. ::

32. አባቴ ጎበዝ ገበሬ ነው_____

A. :: C. ፤

B. ፥ D. ?

33. ሰው ተሰብስቧል_____ ውይይቱ ግን አልተጀመረም።

A. ! C. ፤

B. ፥ D. ::

34. ቶለሳ መጣወይ_____

A. ፤ C. ፥

B. ? D.::

35. ገበያ ሄጄ ስንዴ _____ ጤፍ_____ ባቄላ_____ ገብስና አተር ገዛሁ።

A. ፥ C. ፤

B. :: D. !

መመሪያ ስድስት፡ ከታች ለቀረቡት ፈላጣዊ አነጋገሮች ትክክለኛውን ትረጉም በመምረጥ መልስ/ሽ

36. ነፍስ ዘራ የተሰኘው ፈሊጣዊ አነጋገር

A. ዘሩን አበዛ
C. ልጅ ወለደ
B. ተሻለው
D. በጣም ዳነ

37. ለዛ ቢስ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትረጉም የቱ ሊሆን ይችላል?

A. የማይማርክ
C. የማይስብ
B. የደስደስ የሌለው
D. ሁሉም መልስ ይሆናል

38. ሙያ ቢስ ሲል፡-

A. ፈላስፋ
C.አዋቂ
B. ችሎታ/እውቀት የሌለው
D. ጎበዝ

39. ወላጅ አልባ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትረጉም

A. አባትና እናት የሌለው
C.እህትና ወንወድም የሌለው
B. አክስትና አጎት የሌለው
D. ታላቅና ታናሽ የሌለው

40. ነጋ ጠባ ሲል ምን ለማለት ነው?

A. አልፎ አልፎ
C. ዘወትር
B. አንዳንዴ
D. አንድ ቀን

መመሪያ ሰባት፡- በጅምር የቀሩትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በተለምዷዊ የሚያሟሉትን አባባሎች ምረጥ/ጪ

41. ምን ይሰማ ጆሮ_____

A. ምን ያነሳ እጅ
C. ምንያይ አይን
B. ምን ይውጥ ጉሮሮ
D. ምን ይቅመስ ምላስ

42. _____ በህልሙ ዳውላ ይሸከመል

A. እንቅልፍ የሌለው
C. ራስ ወዳድ ሰው
B. ጠንካራ ሰው
D. ልፋ ያለው

43. ስጋ ቁጥር ቢሉት_____

A. ጣፊያ አንድ አለ
C. ሻኛ አንድ አለ
B. ብሩንዶ አንድ አለ
D. ጉበት አንድ አለ

44. ከልጅ ልጅ ቢለዩ_____

A. ይጣላሉ
C. አመትም አይቆዩ
B. ይረገማሉ
D. አድሎ መስራት ነው

45. ብርሌ ከነቃ_____

A. ይሰነጠቃል
B. አይሆንም እቃ
C. ተወዳጅ ይሆናል
D. ይሰበራል

መመሪያ ስምንት፡- ከቀረቡት አማራጮች ልዩ የሆነውን ምረጥ/ጪ

46.

A. ስንደዶ
B. ጥድ
C. ባህር ዘፍ
D. ዋንዛ

47.

A. ቀበሮ
B. ጥንቸል
C. ዋልያ
D. ውሻ

48.

A. ኮከብ
B. ደመና
C. ፀሐይ
D. ጨረቃ

49.

A. ቀንበር
B. ሞፈር
C. ማጭድ
D. ድግር

50.

A. ሲያየው ተናደደ፡-
B. ሲያየው ተበሳጨ
C. ሲያየው ኑበር ሆነ
D.ሲያየው ተፍነከነከ

ምንባብ አንድ

ችላ ካሉት ከዘነጉት

እድሜን በቅጥ ካልሰሩበት

በለጋ ህይወት ወጣትነት

ምርምሩን ካልጓጉለት

ለስራ ልቀት ካልደከሙ

ለእቅድ ኑሮ ካልሞገቱ

ለመሻሻል ካልዋተቱ

በባዶነት ተፈንጥዞ

በጭፈራ ሆ!ሆ! ብሎ

መስራት ሲቻል ቁልቁል መሄድ

በአጉል ወኔ መስከር ማበድ

ከቀበጠው አብሮ መቅበጥ

ዛሬም ነገም እዚያው መርገጥ

መመሪያ ዘጠኝ፡- ለቀረቡት ጥያቄዎች የግጥሙን ምንባብ ብቻ መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

51. የግጥሙ ምለዕክት _____

A. ጥሩ ውጤት ለማግኘት ቸር መመኘት ይበቃል

B. ያለ አቅም መጠራራት አይገባም

C. ጥረት ካልተደረገ ህይወት ላይ መሻሻል አይመጣም

D. ኩራት ውጤት የስገኛል

52. «እድሜን **<u>በቅጥ</u>** ካልሰሩበት» የተሰመረበት ቃል ፍቺ_____ ነው፡፡

A. ጠንክሮ

B. በአግባቡ

C.በጥሩ ሁኔታ

D. ተጨናንቆ

53. "ዛሬም ነገም እዚያው መርገጥ" የሚለው ስንኝ_____ ይገልፃል፡፡

A. አፍላ እድሜን
B. የቦታ ለውጥ አለመኖርን
C. አለመሻሻልን
D. ሁሉም መልስ ናቸው

54. ግጥሙ ስንት ስንኝ አሉት?

A. አስራ ሦስት
B. ሃያ ስድስት
C. አስራ አንድ
D. አስራ አምስት

ምንባብ ሁለት

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ውበት በገሃድ ሲንፀባረቅ ይታያል፡፡ ሁሉም ገጠር በውበት አንድ ላይሆን ይችላል፡፡ እንደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከተው ቆላማ ገጠሮች ከደጋማ ገጠሮች የተለዩ ናቸው፡፡ ይህንን ጉዳይ በኢትዮጵያ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ ላይ በቂ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይበልጥ ሊያስረዱ ይችላሉ፡፡ በቆላው አካባቢ ሐሩር የበዛባቸው መሬቶች በደጋው አከባቢ ውሃ ገብ ከሆኑት መሬቶች ጋር አንድ አይነት ልምላሜ ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ስለሆነም ከቆላው መሬት ይልቅ ውሃ በመሣብም ሆነ በማመንጨት የደጋው መሬት ሺ ጊዜ እንደሚሻል አጠራጣሪነት የለውም፡፡

«ከቀዳማዊ ትውልድ የአማርኛ ሰዋሰው» በከፊል የተወሰደ፡፡

መመሪያ አስር ፡- በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

55. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛው ሐሳብ የትኛው ነው?

A. ሁሉም ገጠር በውበት የተለያየ ነው፡፡
B. ሁሉም ገጠር በውበት ሊለያይ ይችላል፡፡
C. ሁሉም ገጠር በውበት ተመሣሣይ ነው፡፡
D. መልስ አልተሰጠም፡፡

56. ሐሩር የበዛባቸው መሬቶች የሚገኙት የት አካባቢ ነው?

A. በወይናደጋ
B. በደጋ
C. በቆላ
D. በሁሉም

57. ውሃ ገብ መሬቶች የሚገኙት የት አካባቢ ነው?

A. በደጋ
B. በወይናደጋ
C. በቆላ
D.በሁሉም፡፡

58. “ልመላሜ” የሚለው ቃል ትርጉም ምንድነው?

A. ድርቅ
B. በተፈጥሮ ሐብት የበለፀገ
C.ውህደት
D.ምርት አልባ

59. «ሺ ጊዜ እንደሚሻል» የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል?

A. የደጋው መሬትና የቆላው መሬት ምንም የሚመሳሰሉበት ነገር እንደሌለ

B. የደጋው መሬት ከቆላው መሬት መጠነኛ ልዩነት ያለው መሆኑን

C. የደጋው መሬት ከቆላዉ መሬት እጅግ የተሻለ መሆኑን

D. የደጋው መሬትና የቆላው መሬት መሉ በሙሉ ተመሳሳይ መሆናቸውን

60. ቆላማና ደጋማ ገጠሮች የተለያዩ መሆናቸውን የሚያስረዱት እነማን ናቸው?

A. የየአካባቢው ነዋሪዎች

B. በጉዳዩ ላይ በቂ ጥናት ያደረጉ ምሁራን

C. ተማሪዎች እና አርሶአደሮች

D. ቱሪስቶች

አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የተዘጋጀ የ2010 ዓ.ም የአማርኛ ፈተና የመጠባበቂያ ጥያቄ

ተመሳሳይ ፍቺ ያለውን ቃል ምረጥ /ጭ

1. ዋቢ፡-
   A. ወሬ
   B. ጓደኛ
   C. ዋስ
   D.ቸር
2. አፈላማ፡-
   A. የከብት ጥፋት እዳ
   B. አፈቀላጤ
   C.አፈጉባኤ
   D. አፈጮሌ
3. ገራ፡-
   A. አሳወቀ
   B. አሰለጠነ
   C. ገለጠ
   D. ገላገለ
4. መጋዥ፡-
   A. መጋዝ
   B. ማፈሻ
   C. አጋሰስ
   D. ማንፈሻ
5. ተፈወሰ፡-
   A. ተረዳ
   B. ዳነ
   C. ተገለጠ
   D. ረዳ

ተቃራኒ ፍቺ ያለውን ቃል ምረጥ(ጭ)

6. ፈረጠመ
   A. ጠነከረ
   B. ከሳ
   C. ወፈረ
   D. ደነደነ
7. ተከለ፡-
   A. ከለለ
   B. ወጋ
   C. ነቀለ
   D. ጠወለገ
8. አቆለቆለ፡-
   A. አሻቀበ
   B. አቋረጠ
   C. አጎደለ
   D. አዘቀዘቀ

9. መልከኛ፡-

A. አስቀያሚ
C. ቆንጆ
B. ውብ
D. ገራገር

10. ማርዘም፡-

A. መጨመር
C.ማሳጠር
B. መቀነስ
D. መደርደር